# የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሂድና ስትራቴጂ

ነሃሴ 8፣ 2014ዓ.ም መቐለ

## መግቢያ

ፋሽስት ዐቢይ በትግራይ ላይ የፈጸመውን እልቂት ተከትሎ በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የደረሰበትን ውግዘት ለመቀየር፤ እንዲሁም በየጦር ግንባሮች የደረሰበትን ሽንፈት ለመሸፈን ሰላም ፈላጊ መስሎ በመታየት ሕዝቡን ለማታለል ያዘጋጀው የሰላም አማራጭ ከመጀመሪያውም የማይሆንና የትግራይን ሕዝብ ጥያቄ ፈፅሞ የማይፈታ መሆኑ ቀደም ብሎም የታመነበት ነው። አሃዳዊው መንግሥት በአንድ እጁ የሰላም ባንዲራ እያውለበለበ በሌላ እጁ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ እልቂት አጋዥ ናቸው ያላቸውን ዕቅዶች እያዘጋጀ በመቆየቱ ምክንያት በአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት ላይ የነበረን ተስፋ እንዲቀዘቅዝ አድርጎታል። ስለሆነም፣ ለሁለንተናዊ የመጨረሻ ምዕራፍ ዘመቻ ልንዘጋጅ ተገደናል።

በጦርነት ሂደት ውስጥ የመረጃ ልዕልና ለማግኘት እና በርካታ ሃይሎችን ከጎንህ ለማሰለፍ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ፣ ለዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለህ አስመስለህ እራስህን ማቅረብ መሆኑ ሊረሳ አይገባም። የዐቢይ አገዛዝም ቢሆን አካሄዱ ተመሳሳይ ስለሆነ ቀን ከሌሊት ህልሙና ዝግጅቱ የትግራይን ሕዝብ ማንበርከክ ቢሆንም ነጋ ጠባ የሰላም አማራጭ እያለ ሲለፈልፍ ቆይቷል። የሰላም አማራጭ በሚል ስትራቴጂው፣ በአንድ በኩል ጊዜ ወስዶ ለአጠቃላይ ዘመቻ ለመዘጋጀት በሌላ በኩል ህወሓት ሰላም ፈላጊ አይደለም ብሎ ለዓለም ማህበረሰብ ጥላቻ ለማሰተጋባት እንዲያግዘው በአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት የጀመረው አካሄድ በፍፁም የማያዋጣ ነው።

በተጨማሪም በአደራዳሪነት የተመረጡት የአፍሪካ ህብረት ልዩ መልዕክተኛ ኦሊሴንጎን ኦባሳንጆ፣ ምንም እንኳን ባካበቱት ልምድና በገነቡት ስም የምናከብራቸው ቢሆንም ለዐቢይ አህመድ ባላቸው ፍቅርና እንክብካቤ ሚዛዊነታቸው ጎደሎ ሁኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም በዚህ አይነት አደራዳሪ ሃይል የሚቀርብ የድርድር ነጥብ የትግራይን ህዝብ ፍላጎት አያሟላም። በዚህ ምክንያት የድርድሩ ሂደት የፋሺስት ዐቢይ አህመድን የአገዛዝ ፍላጎት የሚያሟላ በመሆኑ የቀረበውን የሰላም አማራጭ እንደማንቀበል ደጋግመን ለሕዝባችን ገልፀናል። የሕዝባችን ዘላቂ የሰላም ዋስትና የሚረጋገጠው በይምሰል በቀረበው የዐቢይ የሰላም አማራጭ ሳይሆን፣ በክንዳችን ብቻ መሆኑን በፅኑ እናምናለን።

በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና ጭቆና በቀጣይ ማስቆም የሚቻለው፣ የጠየቀውን ያክል የሕይወት መስዋእትነት ከፍለን አዲስ አበባ የሚገኘውን ፋሺስቱን ዐቢይ መንጥረን ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ስንችል ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ የራሳችንና የአጋሮቻችን ዝግጁነት ከመቼውም ጊዜ በላይ በተሻለ ሁኔታ ይገኛል። የውስጥ ትግላችን በማገዝ የሚንቀሳቀሱ እንደ ኦነግ የመሳሰሉ አጋሮቻችን እንዲሁም በተለያዩ የዓለም መአዘናት የሚገኙ የትግራይ ዲያስፖራና ዓለም አቀፍ አጋሮቻችን በዚህ ጊዜ የተሳካ ጥምረት በማድረግ ወደ አዲስ አበባ በምናደርገው እንቅስቃሴ ከጎናችን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን የክልላችን ዋና ስራ አስፈፃሚ በዝግ ባደረገው ውይይት አረጋግጧል። ስለሆነም ይሄ ፅሁፍ ከአጋሮቻችን ጋር የምንከተለውን ስትራቴጂ አስመልክቶ በየደረጃው ለሚገኝ አመራር ግብአት እንዲሆን የቀረበ ነው።

## 1. የሁኔታ ትንተና፤ መልካም እድሎችን ማስፋት እና ፈተናን መቀነስ።

የአማራ ተስፋፊ ሃይል ከፋሽስት ዐቢይ በሚሰጠው ትዕዛዝ መነሻ እና በቆየ የትምክህት ታሪኩ፣ ተስፋፊነቱና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመጫን የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወረራው በላይ የትግራይ ተወላጆችን ስም ማጥፋት፣ የተደራጀ ዘረፋ፣ ግድያና ሴቶችን የመድፈር የመሳሰሉ ወንጀሎችን ፈጽሟል። በዚህም ተስፋፊው የትምክህት ሃይል የትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን ለዓለም አሳይቷል። በአማራ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ሃይሎች ጦርነቱ በፈጠረላቸው አጋጣሚ ተጠቅመው በርካታ ገንዘብ ያገኙ ሲሆን ይህም ራሳቸውን በትጥቅ ያደራጁ ፅንፈኛ ተስፋፊ የአማራ ሃይሎች እንዲፈለፈሉ አድርጓል። ይሄ ሁኔታ የተፈጠረው በሌሎች ክልሎች ቢሆን ኖሮ ለትግላችን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነበር። ነገር ግን ይሄ ሁኔታ የተፈጠረው በአማራ ክልል መሆኑና የተፈጠረው ሃይል የሚታገልበት ዋና አላማው ደግሞ ለትግራይ ሕዝብ ያለው ጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከዚህ ቡድን ጋር ወዳጅነት ሊኖረን አይችልም፤ ይልቁንም ከሁኔታው በመነሳት ቡድኑን በጠላትነት እንፈርጀዋለን።

ይሄ ፅንፈኛ የአማራ ተስፋፊ ሃይል በትግራይ ላይ ካሳየው ጫፍ የወጣ ጥላቻ በላይ፣ በክልሉ ያገኘውን ሕዝባዊ ተቀባይነት ሽፋን በማድረግ እና ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር ከአማራ ክልል መንግሥት የሚስተካከል አቅም መፍጠር በመጀመሩ የዐቢይ አስተዳድር በወሰደው ርምጃ በተወሰነ መልኩ መዳከም ታይቶበታል። አሁንም ግን የዚህ ሃይል አመራሮች በህዝብ ጉያ

ተደብቀው ስለሚገኙ ምቹ ሁኔታ ካገኙ ዳግም ሃይል አግኝተው መነሳታቸው አይቀርም። ይሄ ሁኔታ የትግራይ ሰራዊት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊጠቀምበት የሚገባ ሲሆን፤ ይሄ ሃይል ራሱን "ፋኖ" ብሎ በመጥራቱ የተወሰደበት ርምጃ በርከት ያሉ የአማራ ታጋይ ሃይሎች ከዐቢይ ጎን ተሰልፈው ለመንቀሳቀስ ያላቸውን እንዲቀንስ አድርጎታል። ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ በመስራት የተፈጠረውን መሻከርና ክፍተት የበለጠ እንዲከር ማድረግ ይገባል። ሥራችንን የበለጠ በማጠናከር እና ክፍተቱን በማስፋት የአማራ ሕዝብና ዐቢይ ትግራይን ለመውጋት ዳግም አብረው መሰለፍ ከማይችሉበት ደረጃ ለማድረስ ዘላቂ ቅያሜ እና መራራቅ እንዲፈጠር ማድረግ ለነገ የማይባል ስራ ነው።

በተለይም የልዩነት ነጥቦችን በማህበራዊ ሚዲያ በማጉላት አሃዳዊው የዐቢይ መንግሥት በአማራ ሕዝብ ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት እንዳይኖረው መሸርሸር ያስፈልጋል። በሌላ በኩል፤ ይሄ ጠባብ እና ተስፋፊ ሃይል በፍፁም የትግራይ አጋር ሊሆን እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል። ይሁንና ይህንን እውነታ በገልጽ ባለማሳየት በተመረጡ እና የጋራ ስራ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጥቂት አጀንዳዎች/ስራዎች በጥንቃቄ ሊቀረፁ ይገባል። በግልጽም ይሁን በስውር በፋኖ ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መብዛታቸው የአማራ ክልል መንግሥትን የሚፈትን እንቅስቃሴ ይሆናል፤ ይህም ለትግራይ ካለው ፈተና ይልቅ መልካም እድል ይዞ የሚመጣ አጋጣሚ በመሆኑ ሚዛን የሚደፋ ነው። ስለሆነም ይህ ግንኙነት በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ ወደ አማራ ክልል በተፈናቃይና በተጓዥ ስም የሚገባ ሃይል ሊዘጋጅና ሥራውም በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊፈፀም ይገባል። ይህ ወደ ክልሉ የሚገባ ሃይል በተቻለው መጠን የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቅሞ ወደ አዲስ አበባ ዙሪያም ሊጠጋ ይገባል። አስርገን የምናስገባው ሃይል በየደረሰበት አካባቢዎች መረጃና ሁኔታ የሚጠቁምዋቸው አመራሮች ይኖራሉ። ይህ ስራ ከዚህ በፊት እንዳጋጠመን ታጋያችን ለተልዕኮ ዝቅተኛ ትኩረት በመስጠት በማያስፈልግ የምዝበራና ዘረፋ ተግባር እንዳይሳተፍ ከፍተኛ የሆነ የዲስፕሊን አቅጣጫ ይሰጣል።

በሌላ በኩል የዓፋር መንግሥት የእርዳታ ተደራሽነት በመቆጣጠር በየጊዜው ምክንያት የሌለው ግጭቶች በመፍጠር በአዋሳኝ አከባቢዎች በዘላቂነት ሰላም እንዳይሰፍን በማድረግ በአከባቢው የሚኖሩ ተጋሩ በስጋት ውስጥ እንዲሆኑ አድርጓል። በአወል አርባ የሚመራ ግጭት ቀስቃሽ

ቡድን ከዐቢይ አስተዳድር በሚሰጠው አድናቆትና ቁጥር የሌለው የትጥቅ እገዛ አይኑ የታወረ፣ ጆሮው የተደፈነ በመሆኑ፣ ትግላችን በሚያግዙ የዓፋር የነፃነት ታጋዮችና ቤተሰቦቻቸው አፈናና ግድያ እየፈፀመባቸው ይገኛል።

አምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ፣ ወዳጁ ዐቢይ ለይምሰል የደረበለትን "የሰላም ልኡክ ካባ " ለብሶ መሸፈኛውን ገልጦ ባለፉት ወራት በግልፅ በትግራይ ሕዝብ ላይ አሰቃቂ ወንጀሎችን ፈፅሟል። ይሄ ፍፁም አምባገነን የሆነ የኤርትራ መንግሥት፣ አሁንም እንደ ትላንት ዋነኛ የሰላምና የትግራይ ህዝብ ነፃነት ጠላት መሆኑ ዳግም እያሳየ ይገኛል። ይሄ ጨቋኝ መንግሥት ባጭር ጊዜ መፍትሄ ካላገኘ ሕዝባችንን ወደ ማያቋርጥ ጦርነትና መከራ ዳግም ለማስገባት የሚችል ስጋት በውስጡ የያዘ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች የሚገኙ የዐቢይ ታማኝ አመራሮችና ደጋፊዎች በክልላቸው በምናደርገው እንቅስቃሴ የሚያግዙንን አካላት እያደኑ ማጥቃት ቀጥለዋል።

በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት የትግላችን አጋር መሆኑን በግልጽ ማሳወቃችንን ተከትሎ እንዲሁም በክልሉ ያለው ይዞት እየሰፋ በመምጣቱ የተነሳ ፋሺስቱ ዐቢይ ከሰሜን ግንባር በማያንስ የተጠናከረ ኦፕሬሽን እያካሄደ እንደሚገኝ የፋሺስቱ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን እየተቀባበሉት ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ግንባር ላይ የሚገኙ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት አመራሮች እንደሚነግሩን ከፍተኛ ጉዳት እየደረሳቸው እንዳለና የትግል ስልት መቀየር ግዴታ እንደሆነባቸው ማየት ተችሏል።

ከኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት አመራር ጃል ሚልኬሳ ጋር በሚስጢር ባደረግነው ውይይት፣ ባጭር ጊዜ አመራራቸው ወደሚመች አከባቢ ወይም ወደ አጎራባች ሃገሮች ስልታዊ ማፈግፈግ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዲመቻች፣ እንዲሁም የመከላከል አቅምና ዝግጁነት የሌላቸው የሰራዊቱ አባላት ከተቻለ ዩኒፎርማቸውን ጥለው ወደ ሕዝባቸው እንዲቀላቀሉና እንዲደበቁ ካልተቻለም ለመንግሥት ሃይሎች እጃቸውን መስጠት የተሻለ አማራጭ እንደሆነ አንስቶ ነበር። ይሄ ሃሳብ በጉጂና ቦረና ያለውን ሰራዊት የሚመራው ጃል ገመቹ እና በቤንሻንጉል የሚንቀሳቀሰውን ሰራዊት የሚመራው ጃል ዲናኦል እንደሚመረምሩት የተስማሙ ቢሆንም በማዕከላዊ ዞን ያሉት ጃል ሰኚ ነጋሣና ጃል አብዲ ሰባ ለአዲስ አበባ ካላቸው ቅርበት የተነሳ

ካሉበት አከባቢ ወደ ሌላ አከባቢ መንቀሳቀስም ሆነ ወደ አጎራባች ሃገሮች ስልታዊ ማፈግፈግ የሚለውን ሃሳብ አልተቀበሉትም።

ነገር ግን በወለጋ ያሉ ከኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት አመራር መካከል ጃል ራሣና ጃል ቃንቄ በፋሺስት ዐቢይ ከተከፈተባቸው ከበባ ለመውጣት አስቸኳይ ዘዴ ዘይደው መመርያ በመስጠት ወደሚመች ምስጢራዊ ቦታዎች እንዲንቀሳቀሱ የተደረገው ሙከራ የተሳካ ነው። በዚህ አግባብ በአንዳንድ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት አመራሮች መካከል የትግል ስልት ልዩነት ቢኖርም በአስቸጋሪ ሁኔታ ሁነንም የመረጃ ልውውጣችን እና መተጋገዛችን የሚቀጥል ይሆናል። የዚህ ግንኙነት ዋነኛ መሰረት፣ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት ለአዲስ አበባ ካላቸው ቅርበትና ለሚታሰበው ዘመቻ ከፍተኛ ትግል በማድረግ ድል ሊያስመዘግቡ የሚችሉ በመሆናቸው ላይ ካለን መተማመን የሚመነጭ ነው። በሌላ በኩልም፣ ይሄ ሰራዊት የስትራቴጂያዊ አመራር ክፍተት ያለውና አልፎ አልፎም ከዲስፕሊን ውጪ ግንኙነት በማቋረጥ በራሱ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ከፍተኛ ክትትልና እገዛ የማያስፈልገው መሆኑም ሊረሳ አይገባም።

ከዚህ በተጨማሪ በኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት በአንጃነት የተመደቡ ራሳቸው በአከባቢነትና በሃይማኖት ከፋፍለው የሚንቀሳቀሱ፣ ከሕዝብ ጋር የሚያጣሉ በመጥፎ ተግባሮች ላይ የተሰማሩ ቡድኖች ስለነበሩ ይሄ ሰራዊት በህዝብ እንዲጠላ ቀደም ብሎ ይዞት ከነበረው ቦታዎች በከፍተኛ ኪሳራ እንዲወጡ እየተደረገ ነው። ይሁን እንጂ አሁንም የፋሺስት ዐቢይ አህመድና ሽመልስ አብዲሳን አገዛዝ ሽባ በማድረግ ወደ አዲስ አበባ የሚደረገው የመጨረሻ የትግል ምዕራፍ ላይ የቅርብ አጋሮች እነዚህ የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት በመሆናቸው ሊስተካከሉ የሚገባቸው እና ባለፈው ግምገማ የታዩ ክፍተቶች ታርመው ወደ መጨረሻው ምዕራፍ እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በሱማሌ ክልል ያለው የሙስጠፌ ዑመር አምባገነን አስተዳድር በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የነፃነት ታጋዮችና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማፈኑ እንዳለ ሆኖ፣ የሀገሪቱ የበጀት ቀመር አሰራር ውጭ በዐቢይ ትእዛዝ ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚሰጠው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በክልሉ ያሉትን የትግራይ ተወላጆች እንደሚያሰቃይና ወደማይታወቁ እስርቤቶች እንደሚወስዳቸው የሚያመላክቱ መረጃዎች ደርሰውናል። ይህ አምባገነን ሃይል የአሸባሪውን አልሸባብ እንቅስቃሴ ለመግታት በሚል ምክንያት በርከት ያለ ወታደራዊ ትጥቆች የታጠቀ እና ዝግጅት ያለው

ሲሆን፣ የዐቢይ ሰራዊት በትግራይ ሰራዊት ላይ ባደረጋቸው ዘመቻዎች በንቃት የሚሳተፍ የትግራይ ሕዝብ ጠላት በመሆኑ፣ በክልሉ ከሚንቀሳቀሱ እና የጋራ ጠላታችንን ከሚታገሉ የአልሸባብ ሴሎችና ከኦጋዴን ታጋዮች ጋር የመረጃ ልውውጥ እገዛ እና ስትራቴጂ ሥራዎቻችን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

## 2. ውስጣዊ አቅም ማደራጀት፣ የትግራይን መከላከያ ሃይል ማጠናከር

ባለፉት ወራት ብቻ በርከት ያሉ ጀግኖች ወጣቶች ወደ መከላከያ ሃይላችን እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። ይሄንንም እስከ ቀበሌ ያሉ አደረጃጀቶችን ተጠቅመን ባካሄድነው ስራ የተሳካ ሆኗል። የትግራይ ወጣቶችን አሁን የሚደረገው ትግል ወደ አዲስ አበባ  የመጨረሻ ምዕራፍ ትግላችን እንደሆነ በማሳመን የህወሓት አመራር ካለፈው ዘመቻ ራሱን  ገምግሞ የነበሩበትን ክፍተቶች በሙሉ በመዝጋት ለመንቀሳቀስ ቆርጦ መነሳቱና ድል አይቀሬ መሆኑን መላው የትግራይ ወጣትና ሕዝቡን ለማሳመን የሚያስችል የሚዲያ ሥራ እየተሰራ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የመሳሪያና ትጥቅ አቅም አለማጠናከር ባለፉት ዘመቻዎቻችን የነበረብን ክፍተት እንደሆነ ተገምግሟል። ይህንን ግምገማ በማየት በውጭ ያሉ አጋሮቻችን በአስቸጋሪ እና አጣብቂኝ ጊዜ ውስጥም ቢሆን ችግሩን አልፈው ዘመናዊ ትጥቆች እንድንታጠቅ አድርገውናል። ይህም ሆኖ የዚህ ዘመቻ ምዕራፍ መራርና በርካታ መስዋእትነት የሚጠይቅ በመሆኑ አሁንም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ዘመናዊ ትጥቅ ለመከላከያ ሃይላችን እንዲያቀርቡልን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከውስጥና ከውጪ ተባባሪዎቻችን ጋር ያለንን ስራ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል።

የታጋዮቻችን ትጥቅና ስንቅ የሚሟላት ስራ በዋናነት በነፃነቱ የማይደራደረው ሕዝባችን ተግባር ይሆናል፤  በትግራይ የሚገኙ የዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ሰብአዊ ድጋፍ ማከማቻ መጋዘኖች ፋሽስቱን ለማስወገድ  በምናደርገው ትግል የስንቅ አቅርቦት እንዳይጓደል በቁጥጥራችን ስር ልናደርጋቸው ይገባል። ይሄም ከአለም አቀፍ የእርዳታ አስተባባሪዎች አወንታዊ የሆነ ግንኙነቶች በማጠናከር ረሃብና ተረጅነት ከሕዝባችን ትክሻ ላይ ለማውረድ ለምናደርገው ትግል ደጋፊ እንዲሆኑና ከጎናችን እንዲቆሙ ልናደርግ ይገባል።

አንዱና ዋነኛው የውስጣችን ጥንካሬ መገለጫ ውስጣዊ አቅማችንና የአሸናፊነት ስነልቦና በመሆኑ ይሄን ከፍ የሚያደርጉና የሚያነቃቁ ስልጠናዎችና የዶክመንተሪ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ከሠራዊታችን በተጨማሪ፣ መላው የትግራይ ሕዝብና በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያም ውጪ ለሚገኙ የትግል አጋሮቻችን ድላችን እንደማይቀር እያበሰርን እስከ መጨረሻ መዳረሻችን አብረውን እንዲጓዙ የሚያስችል ስራዎች፣ ስልጠናዎች፣ የመረጃ ልውውጥና ፕሮፖጋንዳ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

በተመሳሳይ በጠላት ላይ ሽብር፣ ፍርሃትና የስነ ልቦና ጫና መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ ሽብር የሚያስፋፉ እና በመሀል ሃገር ያለው ሕዝብ ሳይቀር በመንግሥት አቅም ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር የሚያደርጉ መረጃዎች በሀገር ውስጥና በውጪ ሚዲያዎች በሙሉ ማዳረስ ያስፈልጋል። ለዚህም ባለቤቶቻቸው አዲስ አበባ የሚገኙ ሚዲያዎችና ዩቲዩብ ቻናሎች ከፍተኛ ድጋፍ ስለሚኖራቸው የመረጃና ፋይናንስ ድጋፋችን ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ከሀገር ውጪ የሚገኙ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ሊሂቃን የሚመሯቸው በውጪ ሀገር ያሉ ሚዲያዎች፣ የጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ፀጋይ ርእዮት ሚዲያ፣ የጋዜጠኛ ኤርሚያስ ለገሰ ኢትዮ 360 እና ሌሎች በትግራይ ተወላጆች የሚመሩ ሚዲያዎች ተከታታይነት ያላቸውና በዋነኝነት ፋሺስት ዐቢይ ላይ ያነጣጠሩ የማዳከምና የመበተን ስራዎች ሊሰሩ ይገባል። ይሄም በፓርቲያችን የፕሮፖጋንዳ ክፍል በሚቀረፁ መልዕክቶችና ይዘቶች የሚመራና በላይኛው አመራሮች ክትትል የሚደረግበት ይሆናል።

## 3. ፋሽስት ዐቢይን ለመበተን፣ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ችግሮች ማስቀጠል

በግንባር ላይ ከሚገኘው ድል ባልተናነሰ፣ የጦርነት ነጋሪት በመጎሰምና የተሳካ የፕሮፖጋንዳ ስራ መስራት ብቻውን የሚያደርሰው ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ጠላትን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍሉታል።

ስለሆነም ፋሺስት የዐቢይ መንግሥት በችግር ጊዜ አሳክቼዋለሁ የሚላቸው የእርሻ ዘርፍም ሆነ የኢኮኖሚ ልእልና በማደናቀፍ ወደ ኋላ መመለስ ከተቻለ በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ማድረስ ይቻላል። በዚህም ምክንያት ዐቢይ ያገኘው ጊዚያዊ አንፃራዊ መረጋጋት፣ ሕዝብ በማንቀሳቀስ የጀመረው የእርሻ ልማት፣ ስንዴና ሌሎች የኢኮኖሚ ስራዎች ማደናቀፍ ላይ ትኩረት እናደርጋለን። የእርሻ ዘርፉ እንዲደናቀፍ በየአከባቢው ግጭት በመቀስቀስ እና ግጭት

ለመቀስቀስ የሚያስችሉንን ሃይሎች በማገዝ እረፍት በመንሳት፣ የልማት ስራዎችን ትቶ እሳት ማጥፋት ላይ እንዲጠመድ ማድረግ በረዥም ጊዜ የዐቢይ መንግሥትን ለማዳከም የሚያግዝ ሲሆን፤ ባጭር ጊዜም ደግሞ ለሚካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ የጠላት አቅም እንዲዳከም ትልቅ ጥቅም አለው።

በአማራ ክልል በተወሰነ መልኩም ቢሆን ፊቱን ወደ ልማት ያዞረ ገበሬ እየታየ ነው። ይህ ወደ ልማት ፊቱን ያዞረ ሃይል ትላንት እና ከትላንት ወዲያ የትግራይን መሬት በሃይል የወረረ፣ ሰብል ያቃጠለ፣ ንብረት ያለምንም ይሉኝታ የዘረፈ፣ ሴቶችን የደፈረ ሃይል ነው። ስለሆነም በሕዝባችን ላይ ባደረሰው ግፍ የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድበት ሲገባ የተፈጠረውን ጊዜያዊ ክፍተት በመጠቀም ፊቱን ወደ እርሻው መልሷል፤ ይህ ሃይል የእርሻ ውጤቱን ወደ ቤቱ እንዲያስገባ ልንፈቅድለት አይገባም። ምክንያቱም የእርሻውን ውጤት ወደ ቤቱ ካስገባና በልቶ ከጠገበ ዳግም ወደ ትግራይ መዞሩና የቀደመውን ወንጀል መድገሙ አይቀርም ። ስለሆነም ለጦርነት ባልተዘጋጁበትና በዐቢይ የሰላም ጥሪ በተዘናጋበት ጊዜ አስፈላጊ የሚባል ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ በጦርነት ጊዜ ከእጃችን የወጡ የትግራይ ሕዝብ ታሪካዊና ህገመንግሥታዊ ርስቶች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ታሪካዊ ሃላፊነት አለብን ፣ ብቻውን ሆኖ ለደቂቃዎች እንኳን በፊታችን መቆም የማይችለው የአማራ ክልል ሰራዊት ከየክልሉ በተሰበሰበ ሰራዊት ተከቦ ቢቆምም ከእጁ ላይ የትግራይ መሬቶችን ልናስመልሰው ይገባል። ስለሆነም ከወታደራዊ ዘመቻዎቻችን ጎን ለጎን የቅማንት የወሰንና ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት በሚመለከት እዛ አካባቢ ከፍተኛ ሕዝባዊ ጥያቄ እንዲነሳና አካባቢውን ወደማያባራ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ችግር ሊለውጥ የሚያስችሉ ስራዎች መስራት አስፈላጊ ነው።

አሃዳዊውን የዐቢይ አገዛዝ ከሚቃወሙ ፌደራሊስት ሃይሎች ጋር በተጠናከረ መንገድ ግንኙነታችንን በማደስ፣ በደቡብ ክልል እየታየ ያለውን የክልልነት ጥያቄ በደንብ እንዲጠናከር በማድረግ እንዲሁም ተመሳሳይ የክልልነት ጥያቄዎች በተጠናና በተናበበ መልኩ በሌሎች አከባቢዎች እንዲነሱ በማድረግ አሃዳዊው መንግሥት እየመራው ባለው ሕዝብ የተጠላ መሆኑን ሊያጋልጡት ይገባል።

ፖለቲካዊ አጀንዳዎች በተለይም የማንነት ጥያቄዎች በጥንቃቄ ሊፈቱ የሚችሉበት እድል ከተፈጠረ የዐቢይ አገዛዝ ጎልቶ የሚወጣበት እድል እንደሚኖረው ቀደም ብሎ ከተፈቱ የማንነት ጥያቄዎች ማየት ይቻላል። ስለሆነም፣ ማንኛውንም አይነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ሳንነቅ ወደ አደባባይ እንዲመጡ በማድረግ፣ ጥያቄዎቹ ሕዝባዊ ቁመና እንዲላበሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ጉዳዮች ተገቢ ትኩረት እንዲያገኙ ሚዲያዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች አጀንዳውን የማቀጣጠል ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ በማገዝ የፋሺስት ዐቢይን ውድቀት ሊያፋጥኑ ይገባል።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ልትወጣው ወደማትችለው የኢኮኖሚ ችግር መግባትዋ ቢያሳዝነንም እውነታው ግን ልንክደው የማንችለው እውነት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በርከት ያሉ ዜጎች የኑሮ ውድነቱን መቻል አቅቷቸዋል። ከባድ ፈተና ውስጥ እንዳሉ ብዙ ማሳያዎች አሉ። በትግራይ ያለው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ፋሺስቱ ዐቢይ የትግራይ ሕዝብ በችግር እንዲያልቅ ባለው ፍላጎት እየተቀጣጠለ ቢሆንም፣ ከሌሎች ጦርነት ካላገኛቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከሚታየው ችግር አንጻር ሲታይ እንደሚባለው ሰፊ ችግር እንደሌለ ሊታወቅ ይገባል።

ትግራይ ውስጥ በአንድ በኩል በፋሺስት ዐቢይ የውስጥ ከበባ፣ በሌላ በኩል በጦርነት ቧጫሪው አምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ፣ በመሐል በተስፋፊ የአማራ ሃይል ውስጥ ሆነን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችንን እየታገልን መሆናችንን ማጉላት አስፈላጊ ነው። ከፊታችን ያለው የትግል ምዕራፍ ሕዝባችንን የማዳን ዘመቻ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል። በሌላ በኩል፤ ኢትዮጵያዊያን በተለይም የከተማ ነዋሪዎች፣ መንግሥትን የሚቃወሙት በተለያዩ የፓለቲካ አጀንዳዎች አይደለም፣ ከፓለቲካ አጀንዳዎች ይልቅ በቀጥታ ከዕለት ኑሯቸው ጋር የተያያዘው የኑሮ ውድነት ዋና መንግሥትን የሚቃወሙበት አጀንዳ መሆኑ ግልፅ ነው። ስለሆነም የኑሮ ውድነቱን የሚያባብሱ ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን በተቀናጀ መንገድ መፈጸም አስፈላጊ ነው።

በቀደሙት በኢትዮጵያ የአብዮት ታሪክ በግልጽ እንዳየነው፤ ውስጥ ለውስጥ የተቀጣጠሉ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ወደ አደባባይ የሚወጡትና የስርዓት ለውጦችን እውን ያደረጉት በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ውስጥ ተለንቅጠው ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያ የአብዮት ታሪክ እንዳየነው፤ በዐቢይ መንግሥት ላይ ሕዝብ እንዲያምፅና ፈጣን የስርአት ለውጥ እውን

እንዲሆን ኢኮኖሚውን ማቃወስ ለነገ የማይባል ስራ ነው። የተመረጡ አምራች ድርጅቶችንና መጋዝናቸውን ማጥቃትና ማፍረስ፣ ከእርሻ እስከ ገበያ ባለው ሂደት የዕለት አስቤዛ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዲኖረው ማድረግ፣ ከውጪ የሚገቡ ሸቀጦች እና ነዳጅ እንዲስተጓጎል ዋና ዋና የማስገቢያ ኮሪደሮች በመቆጣጠርና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ችግር እንዲፈጠር እና እንዲባባስ ማድረግ ዋናው ትኩረታችን እናደርገዋልን።

## ማጠቃለያ:-

የትግራይ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ መወሰን የሚያስችለውን መብት ለማግኘት ረጅምና መራራ ትግል የሚጠይቀው መሆኑን ባለፉት አመታት በተካሄደ ትግል ተምሯል። አሁንም በህሕባችን ላይ ያንዣበበው ፈተና እንደ ሕዝብ ካሳለፍናቸው ፈተናዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን፣ የዚህ ትውልድ የትግራይ ወጣትም እንደ ቀደምት ወንድሞቹና አባቶቹ ማንነቱን ሊያስከብርና የሕዝቡ ስቃይ እንዲያበቃ ኃላፊነት አለበት። የትግራይ ሕዝብ በእሳት የተፈተነ ሕዝብ ነው፤ አንበርክክሃለሁ ለሚለው ሃይል እጁን ሰጥቶ አያቅም፣ በስሙና በክብሩ የማይደራደር ሕዝብ መሆኑን ዛሬም በጀግና ልጆቹ ለዓለም ያስመሰከረ ሕዝብ ነው።

እኛ ሰላምን የምናስቀድመው ሰላም የምንወድ ሕዝብ ስለሆንን ቢሆንም፣ ሰላምን ሽፋን በማድረግ እና ሰላምን በመጥራት ብቻ ለሚጠነሰስብን ጥፋት ዝንጉ ስላልሆንን ለይምሰል የቀረበውን የፋሺስት ዐቢይ የሰላም ጥሪ ባለመቀበል ከታሪክ ተጠያቂነት ራሳችን አድነናል።

በመቀጠል ደጋግመን እንደተናገርነው የሚጠብቀን ረጅምና መራር ትግል በመሆኑ ለዚህ የሚመጥን ከወታደራዊ፣ ከስነልቦናዊ፣ ከሎጂስቲክስ በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት አቅጣጫዎች እንደየተጨባጭ ሁኔታውና አደረጃጀታችሁ ተግባር ላይ በማዋል የትግራይን ድል እውን እንድታደርጉ እያሳሰብን፤ ለያንዳንዱ ዝርዝር የተግባር መመርያ ውይይት እየተደረገበት ስለሆነ በየደረጃው ባለው አደረጃጀታችሁ እንዲያቀው ይደረጋል።

**ህልውናችንና ደኅንነታችን በክንዳችን!!**

**ትግራይ ታሸንፋለች !!**